የተወደዳችሁ የሀይማኖት አባቶችና መሪዎች!

የተወደዳችሁ ኢትዮጵያውያን ወገኖች!

ከሁሉ አስቀድሜ በሊቢያ እጅግ አሰቃቂና አረመናዊ ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ በወገኖቻችን ላይ በተፈጸመው ኢ-ሰብአዊ ድርጊት፣ እንዲሁም ደቡብ አፍሪካ በተቀሰቀሰው ዘረኝነት በሞቱት ወገኖቻችን የተሰማኝ ከፍተኛና ጥልቅ ሐዘን በራሴ፣ በኤምባሲው ባልደረቦቼና በቤተሰቤ ስም ለመግለጽ እወዳለሁ፡፡ ይህ አሰቃቂ ጭካኔ የተሞላበት ድርጊት የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት በጽኑ የሚያወግዙት ሲሆን፤ ውግዘቱና ሀዘኑ የኛ ብቻ ሳይሆን የመላው ሰላም ወዳድ ኃይሎችና እምነቶች መሆኑን እየደረሰን ካለው የሀዘን መግለጫ መረዳት ይቻላል፡፡ ሕይወታቸው በዚህ አይነት ዘግናኝ ሁኔታ ለተቀጠፈው ወገኖቻችን ነፍሳቸው እንዲማር፣ ለተጐዱ ቤተሰቦች፣ ወገኖችና መላው የኢትዮጵያ ህዝብ መጽናናትን እንመኛለን፡፡

ውድ ወገኖቼ!

ኤፕሪል 19/2015 በሊቢያ የተፈፀመው አረመኒያዊ ድርጊት የመጀመሪያው ሳይሆን ፌብርዋሪ 2015 በተመሳሳይ በአሰቃቂ ሁኔታ 21 ግብጻውያን ወንድሞቻችን በእነዚህ አሸባሪዎች ተገድለዋል፡፡ ይህ የድርጊቱ ሰለባ በሆኑት ወገኖችና ሀገሮች ብቻ ሳይሆን በሁሉም ሰብአዊ ፍጡር የተቃጣ ጥቃት ነው፡፡ ድርጊቱ በኢትዮጵያ ለዘመናት አብሮ ተሳስቦና ተከባብሮ የኖረው የሀይማኖት መቻቻል ባህል ላይ የተቃጣ ነው፡፡ ዓለም ድርጊቱን አውግዞታል፣ኮንኖታል፡፡ ሰላም ወዳድ መንግሥታትና ዜጐች ድርጊቱን ከማውገዝ በላይ የእነዚህን የጥፋት ተልእኮ ለማክሸፍ በአንድ ላይ መቆም ከመቼውም ጊዜ በላይ ወቅታዊ መሆኑን አበክረው እየገለጹ ነው፡፡

የተፈፀመውን ድርጊት በተመለከተ ከሁሉ አስቀድሞ በሁሉም ሰው አእምሮ የሚነሳው ጥያቄ ለምን የዚህ ዓይነት ጭካኔ የተሞላበት ተግባር ያውም በመገናኛ

ብዙሃን እየታየ ይፈፀማል? የሚለው ነው፡፡ ምንም ዓይነት ምክንያት የዚህን ዓይነት ድርጊት ለመፈፀም መነሻና ምክንያት ሊሆን አይችልም፡፡ ይህ ተግባር እነሱ በሚምሉት የእስልምና እምነት የተወገዘ ተግባር መሆኑን የእምነቱ ተከታዮች በአደባባይ ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል፡፡ ስለዚህ የሃይማኖት ወይንም የፖለቲካ መነሻ ይህን ተግባር ተቀባይነት ያለው ሊያደርገው አይችልም፡፡ ለነገሩ እይ.ኤስ አይ.ኤስ በሚፈፀሙት ድርጊት ከክርስትና እምነት ተከታዮች የእስልምና እምነት ተከታዮችን በበለጠ ሰለባና ተጎጂ እያደረገ እንደሆነ ይታያል፡፡ ለዚህ ነው ድርጊቱ በሁሉም የእምነት ተከታዮች በጋራ የሚወገዘው፡፡ ለዚህ ነው ዛሬ ሰላም ወዳድ ኃይሎች በጋራና በጽናት ይህ ኢ-ሰብአዊና አረመኒያዊ ድርጊት በመቃወም አንድ ላይ የቆሙት፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥት ድርጊቱን ማውገዝ ብቻ ሳይሆን አሁን በሊቢያ፣ በደቡብ አፍሪካ ወይንም የመን ያሉ ወገኖች ወደሀገራቸው እንዲመለሱ በፈቃዳቸው ላይ ተመሥርቶ ከወገኖቻችን፣ ከሚመለከታቸው መንግሥታት፣ ዓለምአቀፍ ተቋማትና ድርጅቶች ጋር በመሆን እየሠራ ይገኛል፡፡ ለተጎዱ ቤተሰቦች መላው ሕዝባችን ከመንግሥት ጎን በመሰለፍ አቅም የፈቀደውን ድጋፍ ለማድረግ እንቅስቃሴ ተጀምሯል፡፡ ሁላችንም ለዚህ ዓላማ የምንችለውን ድጋፍ እንድናደርግ ሁኔታዎች ይመቻቻሉ፡፡ በዚህ አጋጣሚ ጥሪዬን አቀርባለሁ፡፡

ውድ ወገኖቻችን!

አሁን ያለንበት ጊዜ መንግሥታችንና ህዝባችን እንዲሁም ከሀገር ውጭ ያለን ወገኖች ብሔራዊ ሀዘናችንን የምንገልጽበት ጊዜ ነው፡፡ አረመኒያዊ የISIS ድርጊት በጋራ የምናወግዝበትና በቀጣይ ማንም ሰብአዊ

ፍጡር የዚህ ዓይነት ድርጊት ሰላባ እንዳይሆን በጋራ የምንመክርበት፣ የሞቱትን ሰማእታት የምንዘክርብትና ቤተሰቦቻቸውን የምንደግፍበት፣ የምናጽናናበት፣ የጾምና የፀሎት ወቅት ነው፡፡

ይህ ጊዜ ቅን ልቦናና ሕሊና ላለን ሰዎች ሌላ የፖለቲካ አጀንዳ የምናደባልቅበት ጊዜ አይደለም፡፡ የፖለቲካ ልዩነታችን የሞቱትን ሰዎች ሬሳ ሳንቀብር አዳብለን የምናቀርብበት ወቅት አይደለም፡፡ ከዚህ ማንም ጥቅምና ትርፍ ለማግኘት መሯሯጥ ያለበት ወቅት አይደለም፡፡ ይህ የኢትዮጵያዊ ባህል አይደለም፡፡ ይህ ከረዥም ጊዜ ጀምሮ አብሮን ለዘመናት የዘለቀውን የአንድነት እሴታችንን የምናድስበትና በአንድ ላይ የምንቆምበት ጊዜ ነው፡፡ ለዘመናት የቆየውን አብሮነታችን በድጋሚ ለጠላቶቻችንም ሆነ ለወዳጆቻችን ዳግም የምናስመሰክርበት ነው፡፡

ይህ በማንኛውም እምነት የሚደገፍ አይደለም፡፡ ይህ እርስ በርስ የምንናቆርበት ጊዜ አይደለም፡፡ ለሁሉም ጊዜና ቦታ አለና፡፡ ስለሆነም ሁላችንም በአንድነት የምንቆምበት ፈታኝ ወቅት ነው፡፡ይህ ተግባር በጭራሽ መደገም የለበትም የምንልበት ጊዜ ነው፡፡ ዛሬ ይቁም የምንልበት ጊዜ ነው፡፡

ይህን ስናደርግ ብቻ ነው በሥልጣኔያችን፣ በታሪካችንና በባህላችን ልንኮራ የምንችለው፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት በሽብር ተግባር ላይ የተጀመረውን ትግል አጠናክረው በጽናት ለመቀጠል ቃላቸውን በድጋሚ በአደባባይ ገልፀዋል፡፡

ሌላው ንጹሀን ዜጐችን ለንዋየ ፍቅር ብሎ በሕገ ወጥ መንገድ የሚያዘዋውሩት የራሳችን ይሁን የሌሎች ሀገር ዜጐች ከዚህ አስነዋሪና በደም ከጨቀየ ድርጊት እጃቸውን እንዲያነሱ እየጠየቅን ድርጊቱንም በጽኑ እንቃወማለን፣ እናወግዛለን፡፡

በመጨረሻም በድጋሚ የተሰማኝን ጥልቅ ሀዘን እየገለጽኩ፣ ለተጐዱ ቤተሰቦች መጽናናትን እመኛለሁ። ሁላችንም ከጐናቸው መሆናችንን ላረጋግጥ እወዳለሁ። ከዚህ ጋር በተያያዘ ለተጐጂ ቤተሰቦች የሚደረገው ድጋፍ የሚሰበሰብበትን ሁኔታ በቀጣይ የምንገልጽ መሆኑን ለማሳሰብ እወዳለሁ። ዛሬ በኤምባሲያችን ተገኝታችሁ ሀዘናችንን በጋራ ለመግለጽ ለተገኛችሁት ሁሉ ያለኝን አክብሮትና አድናቆት እገልጻለሁ።